# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም ዘወትር አርብ ከ7 p.m. ጀምሮ እየተገናኘን እንጸልያለን። ቃሉንም እንማራለን። በዚህ ፕሮግራም ላይ በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንድንሆን ሁላችንም እንድንሳተፍ ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። በተለያየ ጉዳይ እንዲጸለይላችሁ የምትሹም አገልጋዮችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ!

### የአገልግሎት ሪፖርት

የአገልግሎት መሪዎች የ2017 የአገልግሎት ሪፖርትና የ2018 እቅዶችን ለሽማግሌዎች በጽሑፍ እንድታቀርቡ በጌታ ፍቅር ሽማግሌዎች ያሳስባሉ።

### አገልግሎት

የድምጽና የምዚቃ መሳሪያዎችን በማስተካከል ለማገልገል የምትፈልጉ ዔሊያስን ወይንም ሽማግሌዎችን እንድታነጋግሩ እንጠይቃለን። በሌሎች አገልግሎቶችም ለማገልገል የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን እንድታነጋግሩ እናበራታታለን።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




## "ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።"

(ፊል. 4:13)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**January 28, 2018** | **ጥር 20፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| አምልኮ....................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ............. | ወንድም ብርሃኑ በቀለ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

*“እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፥ አይታከቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደክሙም።”*

(ኢሳ. 40፡ 31)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመነ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**ጸሎት አስተምረን -- ኃይል ለዘላለም የእግዚአብሔር ነው (ክፍል አስራ-ሰባት)**

*“እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።” (ማቴ. 6፡13)*

የአባታችን ሆይ ጸሎት የግዚአብሔርን ስም በመቀደስና መንግስቱን በመፈለግ ይጀምራል። ደግሞም የግዚአብሔርን ዘላለማዊ መንግስት፣ ዘላለማዊ ኃይልና ዘላለማዊ ክብር በማወጅ ይጠቃለላል። ባለፈው ሳምንት እንዳየነው አሁን በምንኖርበት አለም ብዙ መንግስታት ቢኖሩም ሁሉን አሸንፎ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖረው የእግዚአብሔር መንግስት ነው። የመንግስት ጽናትና ጥንካሬ ባለው ኃይል ላይ የተመሰረተ ነው። የእግዚአብሔር መንግስት የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጥበት ነው።

የእግዚአብሔር ኃይል ዘላለማዊ ነው። በአለማችን ታሪክ ብዙ ኃያላን መንግስታት ተነስተዋል። ባቢሎን ኃያል ነበር። ፐርሺያ ኃያል ነበር። ክሪክ ኃያል ነበር። ግብጽ ኃያል ነበር። ወደ ቅርብ ግዜ ታሪክ ስንመጣ ደግሞ እነ ስፔን፣ ፓርቱጋልና ብሪታኒያ ኃያላን ነበሩ። እነኚህ ኃያላን በጊዜአቸው አለምን ያንቀጠቀጡ ቢሆንም አሁን ግን “ነበሩ” በማለት ታሪካቸውን እንዘክራለን። እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ በዙፋኑ ላይ አለ። እርሱ ኃይሉ አይደክምም፤ ማስተዋሉም አይመረመርም። ኢሳያስ በኖረበት ዘመን ብርቱ የነበረው ዖዚያን በሞተበት ጊዜ ነብዩ በሃዘን ሳይመታ እንዳልቀረ ይገመታል። ነገር ግን በዚያው አመት ኢሳያስ እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየው። ነገስታት ቢለዋወጡም፤ ጊዜ ቢያልፍም እርሱ በዙፋኑ ላይ በኃይሉ ይኖራል።

በታሪክ የእግዚአብሔር ኃይል በልዩ ልዩ መንገድ ተገልጿል። ፍጥረት በራሱ የእግዚአብሔርን ኃይል ያሳየናል። ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዳስተማረን የእግዚአብሔር “የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና።” ፍጥረትን ተምልክተን የእግዚአብሔርን ኃይልና ታላቅነት አለማድነቅ አንችልም። ሰው እንኳን በራሱ አስደናቂ ፍጥረት ነው። የእያንዳንዳችን የጣት አሻራ የተለያየ ነው። በውስጣችን ያለው መላዘር (DNA) ቢዘረጋ 10 ቢሊዮን ማይልስ ርዝመት ይኖረዋል። ፍትረተ-አለም ከምንረዳው በላይ ረቂቅና ትልቅ ነው። ለዚህ ነው ዘማሪው ሲዘምር “ስራው እንዲህ ያማረለት እርሱማ እንዴት ውብ ነው” በማለት የተቀኘው።

የእግዚአብሔር የብርታቱ ጉልበት የተገለጠው በፍጥረት ስራ ውስጥ ሳይሆን በማዳን ስራ ውስጥ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደጻፈልን እግዚአብሔር ክርስቶስን “ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል።” ክርስቶስ ከሙታን ሲነሳ ሞት ተረትቷል። ሰይጣን ስልጣኑ ተገፏል። እግዚአብሔር ብቻ ለዘላለም ኃያል እንደሆነ በሰማይና በምድር ሁሉ ተረጋግጧል። አባታችን ሆይ ኃይል ለዘላለሙ ያንተ ነው። አሜን!